በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ፤ በዚህ ታላቅ፤ ሰፊና ታሪካዊ የዮኅተ ሰማይ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ወቅድስት አርሴማ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አንድነት ገዳም ቦታ ላይ ለመሥራት ከታሰቡት የአጭር፤ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ እቅዶች መካከል  የሚከተሉትን በአስቸኳይ  በመሥራት በሰሜን አሜሪካና በሌሎችም ዓለማት ለሚኑሩ ወገኖቻችን የተሟላ መንፈሳዊና ማሕበራዊ አግልግሎትን በመስጠት ለተተኪው ትውልድ የዘለዓለም እርስትና ታሪክ ማቆየት የሚቻል መሆኑን አስቀድመን ማሰብ ከሁላችን ይጠበቃል። በዚህ ታላቅ፤ሰፊና ታሪካዊ የገዳም ቦታ ላይ ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ የሚከተሉትን ታላላቅ ሥራዎችን በሚቀጥሉት ዓመታት በመሥራት ሕዝበ ክርስቲያኑ የተሟላ መንፈሳዊና ማሕበራዊ አገልግሎት እንዲያገኝ ማደረግ የዮኅተ ሰማይ ገዳም ዋና አላማ ይሆናል።

1. **<u>ዘመናዊ ቤተ ክርስቲያን፤</u>**
2. **የማገገሚያ (ሪሀብልቴሽን) ማእከል፤**
3. **ከሁልም የተለየና እራሱን የቻለ የጽሞና ቦታ፤**
4. **<u>ታላቅ ሁለገብ ዘመናዊ አዳራሽ</u>**
5. **<u>የወንድ መነኮሳትና የሴት መነኮሳይት ማረፊያ ቦታና  የልዩ ልዩ አገልግሎት መሰጫ  ክፍሎች፤</u>**
6. **<u>በዚህ አገር የተወለዱ ሕጻናትና ወጣቶች የሀገራቸውን ቋንቋ፤ሃይማንቶ፤ባሕልና ታሪክ በሚገባ እንዲያቁ በማድረግ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን እንዲረከቡ የሚያደርግ ቋሚ የትምሕርት አሰጣጥ ፕሮግራም መዘርጋት፤</u>**
7. **ዘመናዊ ዩኒቨርስቲ፤**
8. **የተሟላ አገልግሎት የሚሰጥበት ሆስፒታል፤**
9. **የጸበል ቦታ፤**
10. **<u>በአረፍተ ዘመን የሚገቱ ወገኖቻችን ለዘለዓለም የሚያርፉበት ደረጃውን የጠበቀ የቀብር</u> ቦታ፤**
11. **የካህናት ማሰልጠኛ ኮሌጅ**
12. **የአብነት ትምሕርት ቤት (የዜማ፤የቅኔ፤ የቅዳሴ፤ የአቋቋና የመጻሕፍት ትርጓሜ፤**
13. **ሰመር ካምፕ (ታዳጊ ሕጻናት ለአጭር፤ለመካከለኛና ለረጅም ጊዜ የሚማሩበት)**
14. **የበጎ አድራጎት ድርጅት፤**
15. **የእደ ጥበብ/ የቅርሳቅርስ ድርጅት፤**
16. **የሽመና ሥራ ድርጅት፤**
17. **የልብስ ስፌት ድርጅት፤**

18. ቤተ መጻሕፍት/ ሙዝየም፤

19. የምርምርና ጥናት ቦታ ማዕከል፤

20. መንፈሳዊ የጉዞ ወኪል(የኆኅተ ሰማይ አንድነት ገዳም መንፈሳዊ የጉዞ ማሕበር)

21. ለገዳሙና ለአጥቢያ አብያተ ክስቲያናት ቋሚ የገቢ መንጭ የሚያስገኝ የልማት ሥራ ዎችን መዘረጋት፤

ሀ. የወይን ተክል ልማት፤

ለ. የወይራ ዘይት ልማት፤

ሐ. የቀንድ ከብቶች እርባታ ፤

መ. የበግና የፍየል እርባታ፤

ሰ. ይንብ እርባታ፤

22. ገዳሙ ዘመኑን የዋጀ አገልግሎት እንዲሰጥ ቋሚ የመገናኛ ብዙኃን/ ሶሻል ሚዲያ (ኆኅተ ሰማይ ሚድያ)

23. የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምባቸውን መጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት፤

24. የበጎ ፈቃድ አገልግሎት(የምክርና የልዩ ልዩ ማሕበራዊ አገልግሎት መስጫ ማእከል)
25. የአዳሪ ትምሕርት ቤት